## 1. የተለያዩ የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ፍቺዎቻቸው

| | |
|---|---|
| 1. | ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ ላይ አይወጣም። <br> • ባንድ ጊዜ ሁለት ነገር ማከናወን አስቸጋሪ ነው። |
| 2. | ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ። <br> • ከብዙ ደካሞች አንድ ጉበዝ ይበልጣል። |
| 3. | ላም አለኝ በሰማይ፣ ወተቷንም አላይ። <br> • ተጨባጭነት የሌለው ተስፋ። |
| 4. | መጫር ያበዛች ዶሮ መታረጃዋን ካራ ታወጣለች። <br> • አጉል ጥጋብ በራስ ላይ ችግር ያስከትላል። |
| 5. | ጽድቁ ቀርቶ ምነው በወጉ በኰነነኝ። <br> • ምነው ጭማሪው ቀርቶ ዋናውን ባገኘሁ። |
| 6. | (ሀ) ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ (ለ) ቀና ሲታጣ ይመለመላል ጉባጣ። <br> • ዓዋቂዎች በሌሉብት ትንሽ የተማረውም እንደ ዓዋቂ ይቆጠራል። |
| 7. | ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ። <br> • ከብዙ ደካሞች አንድ ጉበዝ ይበልጣል። |
| 8. | ረጅም ጦር ባይወጉበት፣ ያስፈራሩበት። <br> • ታዋቂ ዘመድ መመኪያ ነው። |
| 9. | ሲያጌጡ፣ ይመላለጡ። <br> • ለማጌጥ ሲባል ራስንም መጉዳት አለ። |
| 10. | (ሀ) ሥራ ለሠሪው፣ እሾህ ለአጣሪው። (ለ) በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም። <br> • ተንኰለኛ በተንኰሉ ይጠፋል። |
| 11. | በሬ ሆይ ሣሩን አየህና ገደሉን ሳታይ። <br> • ጥቅሙን ብቻ ሳይሆን ጉዳቱንም አስተውል። |
| 12. | አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም። <br> • ዘመድ ከዘመድ ቢጣል አይጠቃቃም። |
| 13. | (ሀ) ዓባይን ያላየ ምንጭን ያደንቃል። (ለ) ለቆማጣ አንድ ጣት ብርቁ ነው። <br> • አይቶ የማያውቅ በትንሹ ይገረማል። |
| 14. | የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል። <br> • ትዕግሥተኛ ሰው ከፈለገበት ዓላማ ሊደርስ ይችላል። |
| 15. | ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው። <br> • ትችት ቀላል ሲሆን መሥራት ግን ከባድ ነው። |

*ጥንቅርና ዝግጅት፡- ዶ/ር አንበሴ ተፈራ*